መጋቢት ፲ ቀን ፳፻ ዓም(ማርች 19 2008)

## <u>ወይ ኑሮና ዘንድሮ !</u>

**<u>ከአያልነሽ</u>**

**የገንዘብ ወይስ የሥልጣን ስግብግብነት ወይስ የሥልጣን ጥመኝነት? በአቋራጭ ሚሊየነር ለመሆን፣ ወይስ በአቋራጭ ሥልጣን ላይ ቁጢጥ ለማለት? ወይስ የገንዘብ ስግብግብነትና የሥልጣን ስግብግብነት "የጋራ ግንባር"። ይልና ቀርጠ ቀጥሎ ሪፖርተር ጨዋታዬን አሳመርኩ ብሎ ደግሞ እንዲህ በማለት ይተረትራል። የገንዘብ ስግብግብነት እንዳለ የተረጋገጠ ነው። ከበስተጀርባውስ የፖለቲካ ስግብግብነትና የሥልጣን ጥመኝነት ግፊት እያደረገ ነው? ነው ጥያቄው እንጅ በ1 ሰዓት ውስጥ በስልክም፣ በሌላም በሌላም የተሰራጨው የጨው መልዕክት፣ በአንድ ጊዜ ከመደርደሪያ የተነሳው በነጋዴ ብቻ ሳይሆን ከበስተጀርባው ሌላ እንዳለ አሳማኝ ምልክት ነው። (ሪፖርተር ማርች 12/2008)**

**እኔ በይዘቱ ላይ ነውና የማተኩረው የወያኔ አፈቀላጤ የሆነው ሪፖርተር፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን በሚታየው የኑሮ ውድነት ሳብያ፣ በመሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ላይ በወረደው መዓት ላይ፣ ይህንን ሕዝብን በኑሮ ውድነት እየፈጀና እየቀጣ ያለውን የደደቢት ተምች ፊት ለማዳን፣ ወግ አሳመርኩ ብሎ በጋዜጣው ላይ የዘገበው ነበር ። ለዘገባው የሰጠው ርዕስ ደግሞ "የወጥ አብዮት" የሚል ነው። ከአዛዣቸው የሚወርሱት ቃል ነውና ወዲያው "እሳቸው" ከአፋቸው እንዳወጧት ቀጨብ አድርገው ይወስዱና ያንኑ ወስደው ድረ ገጾቻቸውንና ጋዜጦቻቸውን ያሸበርቁበታል። ይዘት ላይ ምርምር፣ ጥያቄ የለም፤ የድንጋይ ዘመን ሰዎች ስለሆኑ መመራመር አይገደዱም። መጠየቅ፣ ለማወቅ መጣር እነርሱን አይመለከትም። እንደወረደ መዋጥ። ለምንስ ያስቡ? ለምንስ ይመራመሩ? ለምንስ በምርምርና በመጠየቅ እንቅልፍ ያጣሉ? ማሰብ መመራመር የሰብዕና መገለጫ ናቸው። አቦ! አሁንስ እኔም ምርምርን እንደወዲያኞች ልርገመው፡፡ ምርምር ነፍስህ አይማር ብያለሁ ዘመዴ። ጉድ ነው በምርምር መሰቃየት። እንደ ወያኔ ለጥ ብሎ እንደምብላት**

**ለሕዝብ ኑሮ ተወደበትና የዋጋ ግሽበት እላይ ተሰቅሎ ፣ አገዛዝህ በቅቶኛል፣ "የምበላው ባጣ ልጄ ጥርስ አወጣ" ሆኖ እያለ ነገሩ ሁሉ፣ ብርቱካኑን ሳያገኝ "ብርቱካን አብዮት" ብሎ "ሲራቀቅና" ሲመራመር ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እግር ከወርች የታሰረውና የወያኔ እዳ ከፋይ የሆነው ። ወይ ዘንድሮ! "ብርቱካናማው አብዮት" (ኦሬንጅ ሪቮሊሽን) "ቀዩ አብዮት" (ሬድ ሪቮሊሽን) የሚለውን ለገሰ ዜናዊ ሲናገር ከአፉ ነጥቀው ዋልታና ዓይጋ ያኔ እንዳስተጋቡት አይነት መሆኑ ነው። ከዚያ በኋላማ አለቀ ደቀቀ። ለዓለም መንግሥታትና ለዓለም ሕዝብ ሁሉ "አቤት ንግግር" አለባበስ እንደ ወግደርስ እና አነጋገር እንደ ሺዋንዚንገር እንደተባለው ዓይነት ለገሰ ዜናዊ ሲናገር በቃ ተከተተ ይባልና ሲቪሊቲ ሩም የለገሰ ንግግር "የጥናት መጽሔት" ሆኖ ይወርዳል። ከዚያ በኋላማ..........**

**በጄ! ሪፖርተር "የወጥ አብዮት"! እና ምን ይሁን ታዲያ? አቦ! እነኝህ ሰዎች አይገባችውም እንዴ? አሁን እኮ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለው**

በኢትዮጵያ ሕዝብና በወንበዴው አገዛዝ ወያኔ መካከል፤ ባለው ቅራኔ ምክንያት የሚደረግ የፖለቲካ ትግልና ፍጥጫ ነው። ስለዚህ ሪፖርተር ሆይ! እባክህ ከጀርባው ምን ይኖረው ይሆን ብሎ መጠየቅን ምን አመጣው? በድጋሚ ሪፖርተር ሆይ! ምንም ይሁን ምን ጉዳዩ ለእናንተና ለወንበዴው አገዝዝ ግልጽ ሳይሆን ቀርቶ ከሆነ፣ አሁንም እደግመዋለሁ፣ በቅርቡ ''እንማማር ብለው''የለ ፕሮፌሰር መስፍን፣ ትግሉ በወንበዴው ወያኔና በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የሚደረግ የሥልጣን ግብግብ ነው። ወያኔ የተቀመጠበት ዙፋን መጀመሪያውኑም ለእርሱ ሊሆን የማይገባና አሁንም ሥልጣኑን እንዲለቅ የሚጠይቅ የፖለቲካ ፍጥጫ ነው - አራት ነጥብ። በቀላል አማርኛ ወያኔ ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ከቀን 1 ጀምሮ (ከገባበት ጊዜ ጀምሮ) እስከአሁን ድረስ ብቃትና ችሎታ ያልነበረውና የሌለው መሆንን ተፈትኖ በዓለም ፊት ፈተናውን ወድቋል። ግን የደደቢት ምሩቅ ነውና ምንድን ነው የሚባለው .....ጠፋብኝ፣ አዝናለሁ። ኢትዮጵያኖች እንዲህ አይነት ነገር ሲያጋጥማቸው የሚሉት ነገር አለ፣ አሁን ለጊዜው ዘነጋሁት ካስታወስኩት ግን እነግራችኋለሁ። አንድ ነገር ግን ልበላችሁ። እኔ ብታምኑም ባታምኑም የወያኔ ነጋሪት ጋዜጣ የሆኑትንና የወያኔ ድረ-ገጾችን ስጎበኝ፣ ሁልጊዜ ሳቁ ይመጣብኛል። ምክንያቱም አንድ መስመር እንዳነበብኩ መደምደሚያው ምን እንደሆነ ስለምረዳ ማለት ነው። ከዚያ ባሻገር ደግሞ ለእነ አባ መላና ለአባ መላ ''ጸዓዳይ ወያኔነታቸውን ለማረጋገጥ'' የሚራኮቱ ምስኪን ልጆችን ሳስባቸው ደግሞ አዝናለሁ። ነጭ ወረቀት ማለት ናችው። የተሰጣቸውን ያለምንም ጣጣና ምርምር መውሰድ። እስቲ እነኝህ ምስኪኖች ምን እንደሚወስዱ ላሳያችሁ። አሁንም ከሪፖርተር እነሆ!

በሌላ የፖለቲካ ቅስቀሳ ተደራጅቶና አደራጅቶ በተለይም ''ተቀናጅቶ'' ለመታገል ወኔውም፣ አመለካከቱም፣ አቅሙም ሲጠፋና ህዝቡ አልገባም ሲል ''በወጥ'' በኩል ገብቶ ህዝቡን ለማነሳሳት መሞከር ያለ ይመስላል፤ ''የወጥ አብዮት'' ያልነውም ለዚህ ነው። ''ቀዩ አብዮትና'' ''ብርቱካናዊው አብዮት'' አልሳካ ሲል በጨውና በበርበሬ በኩል ''የወጥ አብዮት'' እየተሞከረ ይመስላል ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል።

''የወጥ አብዮት'' አያሳቅም? እኔ በጣም ነው የሚያስቀኝ። ''የትዕግስት አብዮት'' ወዘተ....የሚባል ደግሞ እየወጣ ነው ከመለስ አንደበት፣ አሁንኑ ወደኛ ይደርሳሉ። ልክ ''እንደመቻቻል ትግል'' ወይም ''መችቻል ይቻላል'' አይነቱ ቃል። ሰሞኑን ከወያኔው/ህወሓት ቁንጮ የሚዥጎደጎዱ ቃሎች በዝተዋልና። ይሁን ግድ የለም፣ ግን በቁም ነገር ለሚመራመር ሰው በዚያኛው አብዮት ''አልነሳም ወይ አልገባም ሲላቸው'' የተባለው ህዝብ ''በወጡ አብዮት'' ግን ሊያጠምዱት እየተራወጡ ነው ብሎ ማልቀስንና መጨሁን ምን አመጣው ታዲያ? ''ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል'' የሚል ዋይ ዋይታና ማስጠንቀቂያስ ለምን አስፈለገ? የአባ መላ ምስኪን ልጆች ይሄ አይታያቸውም? አይጠይቁም ? ዝም ብለው መኮልኮል ወይ መታደም ነው። ለዚህም ነው ምስኪኖች የምላቸው። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ጣሪያ ነክቶ የወያኔ ራዲዮኖች፣ ድረ ገጾች፣ የወያኔ ጋዜጠችንና የወያኔ ልሳን የሆነው ዋልታና ራዲዮ ፋና እያስተጋባው ያለውን ሃቅ፣ መለስ ዜናዊን እንቅልፍ ነስቶት

ለፓርላማ ተብየው ያሰማውን ኑዛዜ እንኳ መመልከቱ ብቻ በቂ ነው። ይህንን ቁጣና ዛቻ የቀላቀለውን የፓርላማ ውሎ ተመልከቱ። (ማርች 18/2008)

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የጨው ዋጋ 1 ብር ከ50 ሳንቲም ሲሸጥ የነበረው በአንዴ 10 ብር ሲገባና ሲቸበቸብና፣ እስከ 12 ብር ድረስ የደረሰ መሆኑን ሪፖርተር ራሱ ዘግቦታል። የጤፍ ዋጋ 750 ብር፣ 1 ኪሎ የተፈጨ በርበሬ 50 ብር፣ 1ኪሎ ቡና 35 ብር፣ 1ሊትር ዘይት 35 መድረሱን ፓርላማ ተብየው ውስጥ ሲነገር ላዳመጠ፣ የእነ ሪፖርተር ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ውነት በዋጋው ግሸበት ሕዝቡ የሚኖርበት የስቀቃ ኑሮ አስጨንቋቸው ወይስ ይህ በቋፍ ላይ የሚገኝ ሕዝብ ለማይቀረው አመጽ መቀስቀሱ አይቀሬ መሆኑ ስጋት ላይ ጥሏቸው? ጉደኛው ሪፖርተር ይህንን ስጋቱንና አይቀሬውን የህዝብ ቁጣና አመጽ፣ እንደለመደው የሕዝብ ቁጣና አመጽ የሌለ ለማስመሰልና ራሱን ሲያታልል እንዲህ ይላል ሪፖርተር፥

> ስለሆነም "የወጥ አብዮት" ሕዝብ በመንግስት ላይ እንዲነሳ ያደርግልናል ብለው ተስፋ የሚያደርጉ ካሉ፣ ሕዝብ በዚህ አትምጡብኝ ብሎ በነሱ ላይ ሊነሳ እንደሚችል ቢገነዘቡት ይበጃል። ሥልጣን ይገባኛል የሚል ካለ ፕሮግራሙንና መርሃ ግብሩን አስተካክሎ በአደባባይ ትግሉ ይምጣ እንጅ "በወጥ ቤት" በኩል ሊሸሎከለክ አይገባም።

አይ! ሪፖረተር። ቅዥት ወይስ የደደቢት አብዮት! ወይ ኑሮና ዘንድሮ።

ይቅርታ ወድ አንባቢዎች! ቀደም ሲል መግቢያዬ ላይ ኢትዮጵያኖች እንዲህ አይነት ዓይን ያወጣ ነገር ሲያጋጥማቸው የሚሉት ነገር አለ ብየ ያለፍኩት ነገር ነበር ካስታውስኩት እንግራችኋለሁ ያልኩት፤ አሁን አስታወስኩት። ምን መሳላችሁ እንዲህ አይነቱን የእነ ሪፖርተርና መሰሎቻቸው ዓይን አውጣነትን ፈጣጣ ይሉታል።

እስቲ ደግሞ ተመራመሩ ቀደም ሲል ምርምርን ብረግመውም፣ የማያስብ፣ የማይመራመር ደግሞ ድንጋይ ይባላልና ድንጋይ ላለመባል የምርምር ሥራ ልስጣችሁ። የጨው ዋጋ 1ብር ከ 50 ሳንቲም ሲሸጥ የነበረው፣ በአንዴ 10 ብር መደረሱ ብንመራመር የጨው ነጋዴ ባለሃብትና ሚሊየነር፣ የወዲ ዜናዊ ሌላኛው ልጅ ኒቆዲሞስ ዜናዊ የጨውን ጀኒያ/ከረጢት አስረውት ይሆን ? አባ መላ እባክህ ጠይቅልን? ማይክ ፍሪ  አባ መላ አመስግናለሁ።

የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሰሩ የፖለቲካ እሥረኖች በሙሉ ይፈቱ!

ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኑር!

ቸር ይግጠመን